

# የስደተኛ ዝግጅት ፓኬት

*በኮሎራዶ የስደተኛ መብቶች ጥምረት*

የተሻሻለው ጃንዋሪ 2025 |

2525 W Alameda Ave
Denver, CO 80219 (303)
922-3344
coloradoimmigrant.org

# መግቢያ

- *ይህ ፓኬት ከዩኤስኤ መባረርን ለመከላከል የታሰበ አይደለም። ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች (ማለትም ፈቃድ ያላቸው የኢሚግሬሽን ጠበቆችን) በማነጋገር ምክር እና እርዳታ መጠየቅ አስፈላጊ ነው።*

- *የዚህ ፓኬት አላማ ቤተሰብ የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ በሚገጥመው ጊዜ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የግል መረጃዎቻቸውን እንዲያደራጁ በመርዳት የደህንነት ስሜትን ማሳደግ፣ የቤተሰብ መረጋጋትን ማሳደግ እንዲሁም የአዕምሮ ጤናን ማሳደግ ነው።*

- *በዚህ ፓኬት ውስጥ የተካተቱት መረጃዎች እና ቅጾች የተሟሉ እና ትክክለኛ ስለመሆናቸው የተገለጸ ዋስትና የለም። እዚህ የቀረቡት ሁሉም ቅጾች ሊለወጡ ይችላሉ እናም ለወደፊቱ ማንኛውንም ለውጦች ለማንም የማሳወቅ ግዴታ የለም። በግለሰብ ፍላጎቶች ላይ በመመርኮዝ ቅጾች አርትዖት ሊደረግባቸው፣ ሊሻሻሉ እና ሊሰፉ ይችላሉ።*

- *ሁሉንም መረጃዎች ካገኙ ይህንን ፓኬት ለመሙላት ከሁለት እስከ አራት ሰዓታትን ይወስዳል። ከቤተሰብ፣ ከጓደኞች እና ከባለሙያዎች ጋር የሚደረግ ውይይት ብዙ ሳምንታትን ወይም ወራትን ሊወስድ ይችላል። ሁልጊዜ ፓኬትዎን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ለማስቀመጥ ይጠንቀቁ። ፓኬቱን ኮፒ ማድረግ እና ለታመነ ሰው መስጠት ጥሩ ሀሳብ ነው።*

- *ይህ ፓኬት እርስዎ እና ቤተሰብዎ በኢሚግሬሽን ባለሥልጣናት ሊወሰድ ለሚችል እርምጃ እንዲዘጋጁ ይረዳዎታል። ይህ ፓኬት ለማንኛውም ዓይነት አገልግሎት ወይም እርዳታ ማመልከቻ አይደለም። በምትኩ፣ የእራስዎን እቅድ እና ዝግጅት ለመምራት እንዲያግዝዎት የሚሞሉት መርጃ ነው። ይህንን ፓኬት በመሙላትዎ፣ ወድያውኑ ከህግ ባለሙያ ጋር እንዲገናኙ አይደረጉም። አንድ ጠበቃ ወይም ሌላ የሕግ ባለሙያ ማነጋገር የእርስዎ ኃላፊነት ሲሆን እኛ ይንኑ እንዲያደርጉ በጥብቅ እንመክራለን። ገጽ 46 በኮሎራዶ ውስጥ ያሉ የአንዳንድ የኢሚግሬሽን ጠበቆች ስም እና የግንኙነት መረጃ ይዘረዝራል።*

- *በዚህ ፓኬት ውስጥ ያለው መረጃ በጣም ጥንቃቄ የሚፈልግ ነው። ከመቀጠልዎ በፊት፣ እባክዎን ለማስቀመጥ ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ እንዳለዎት ያረጋግጡ። ይህ ከታመነ የቤተሰብ አባል ጋር፣ በካዝና ውስጥ ወይም በሌላ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፣ ለተጨማሪ ደህንነት እና ተደራሽነት ቢያንስ አንድ ሌላ የታመነ ሰው የዚህን ፓኬት ቦታ ማወቁ አስፈላጊ ነው።*

# ማውጫ

***ክፍል 1፡- ይህንን ፓኬት ለማዘጋጀት የሚረዳ መረጃ (ገጽ 4-5)***

***ክፍል 2፡- መረጃ እና እውቂያዎች (ገጽ 6-13)***

1. *የድንገተኛ ጊዜ ቡድን*
2. *ጓደኞች እና ቤተሰብ*
3. *የማህበረሰብ መርጃዎች*
4. *በአሜሪካ ውስጥ ያለ ቤተሰብ*
5. *ከአሜሪካ ውጭ ያለ ቤተሰብ*
6. *ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች መረጃ*

***ክፍል 3፡- የቤተሰብ እቅድ (ገጽ 14-22)***

1. *ለልጆች*
2. *ባል፣ ሚስት ወይም ኢጋር ከተወሰደ*
3. *ሁለቱም ወላጆች ከተወሰዱ*
4. *ቤት፣ አፓርታማ፣ ተጎታች*
5. *መኪና፣ የጭነት መኪና*
6. *የመገልገያ ሂሳቦች*
7. *የቤት ዕቃዎች እና ሌሎች ንብረቶች*
8. *ህጋዊ እርምጃ*
9. *ሌሎች መመሪያዎች*

***ክፍል 4፡- መታወቂያ እና ሰነዶች (ገጽ 23-28)***

1. *የውክልና ቅጾችን በተመለከተ አስፈላጊ ማስታወሻዎች*
2. *ማስጠንቀቂያ እና ግልጽ የኃላፊነት መልቀቂያ*
3. *የውክልና ቅጾች*

a. *ዓላማው የተወሰነ ውክልና መመሪያዎች*
b. *ዓላማው የተወሰነ ውክልና*
c. *ለልጆች የሚሰጥ ፈቃድ ቅጾች መመሪያዎች*
d. *በወላጅ ወይም በአሳዳጊ የሚሰጥ የውክልና ስልጣን*

*የሚከተሉትን በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰነዶችን ያስቀምጡ፡-*

- ❑ *የልደት የምስክር ወረቀት (ዋናው እና ፎቶ ኮፒ)*
- ❑ *መታወቂያ (የኮሎራዶ መንጃ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ፣ ሌሎች መታወቂያዎች)*
- ❑ *የክትባት መዝገብ (ዋናው እና ፎቶ ኮፒ)*
- ❑ *የቤተሰብ ፎቶዎች እና (4) የፓስፖርት ፎቶዎች ለመላው ቤተሰብዎ*
- ❑ *የውክልና ስልጣን*

## ክፍል 5፥- ሌሎች የግል ሰነዶች (ገጽ 29-30)

የሚከተሉትን በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰነዶችን ያስቀምጡ እና ሲካተቱ ሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ፥-

- ❑ በአሜሪካ ውስጥ ስለመኖር የሚያሳዩ መዝገቦች
- ❑ የሊዝ መዝገቦች
- ❑ የክፍያ ወረቀቶች
- ❑ የትምህርት ቤት መዝገቦች
- ❑ መግለጫዎች፣ ሂሳቦች፣ ደረሰኞች
- ❑ የሕክምና ሂሳቦች
- ❑ አሜሪካ ከገቡበት ቀን ጀምሮ አሜሪካ ውስጥ ስለመኖር የሚያሳዩ ሌሎች ቀን የተጻፈባቸው ሰነዶች
- ❑ የኢሚግሬሽን መዝገቦች (የሚመለከተው/የሚገኝ ከሆነ)
- ❑ የኢሚግሬሽን ማመልከቻዎች፣ የፍርድ ቤት ሂደቶች፣ የICE ሂደቶች
- ❑ የአሜሪካ የወንጀል መዝገቦች (የሚመለከተው/የሚገኝ ከሆነ)
- ❑ በየወንጀሉ ስለተፈረደ ፈርድ የተረጋገጠ መዝገብ
- ❑ በአሜሪካ ውስጥ ለሁሉም ዓመታት ለቀረቡ ግብሮች የአሜሪካ የግብር መዝገቦች
- ❑ ደብዳቤዎች

## ክፍል 6፥- ሌሎች ሰነዶች እና መረጃዎች (ገጽ 31)

- ❑ ቁጥጥር ስር ካዋሉ ምን ማድረግ እንዳለብዎት
- ❑ ታሪክዎን ሪፖርት ያድርጉ
- ❑ እስረኛውን እንዴት ማግኘት እና ማስያዣ መክፈል እንደሚቻል
- ❑ ለኢሚግሬሽን ጠበቃ የሚቀርቡ ጥያቄዎች
- ❑ በኮሎራዶ ውስጥ ያሉ ጠበቆች
- ❑ መብቶችዎን ይወቁ
- ❑ የአሜሪካ ፓስፖርት ማመልከቻ

# ክፍል 1
# *ይህን ፓኬት ለማዘጋጀት የሚረዱ መረጃዎች*

*ፓኬቱን በእራስዎ ለመሙላት መዘጋጀት ወይም ማሰብ ያለብዎት አንዳንድ ነገሮች አሉ።*

*ከቤተሰብዎ ጋር ይወያዩ፡-*

- ❑ *በእርስዎ ህይወት ውስጥ ማን ለእነዚህ ኃላፊነት ሊወስድ ይችላል፡- ልጆች፣ የሂሳብ ክፍያዎች፣ ንብረት… ከታሰሩ? የምያምኑት ሰው መሆን አለበት። ብዙ ሰዎች እንደ መጠባበቂያ መኖራቸው (ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ ካህናት፣ ጎረቤቶች፣ ወዘተ.) ጥሩ ነው። የእውቂያ መረጃዎቻቸውን ያግኙ።*

---

*በዚህ ፓኬት ውስጥ ላሉ ህጋዊ ቅጾች የሰነድ ማረጋገጫ አገልግሎቶች ከፈለጉ፣ ሰነድ አረጋጋጩን ሲጎበኙ ከመታወቂያ ሰነዶችዎ ውስጥ አንዱ ይኑርዎት፡-*

- ❑ ***መታወቂያ*** *- አንድ ብቻ ነው የሚያስፈልገው*
- ❑ *መንጃ ፈቃድ፣*
- ❑ *የብሄራዊ መታወቂያ ሰነድ (ለምሳሌ፡- የቆንስላ መታወቂያ)*
- ❑ *ዜጋ ያልሆነ ሰው የነዋሪነት ካርድ*
- ❑ *ፓስፖርት*
- ❑ *ከኮሌጅ ወይም ከትምህርት ቤት የሚሰጥ መታወቂያ*

*እነዚህን ሰነዶች ይሰብስቡ እና በዚህ ፓኬት ጋር ያስቀምጡዋቸው፡-*

- ❑ *የክትባት መዝገቦች (ዋናው እና ፎቶ ኮፒ)*
- ❑ *የቤተሰብ ፎቶዎች እና (4) የፓስፖርት ፎቶዎች ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል*
- ❑ *የባንክ፣ የሞርጌጅ እና የኪራይ መረጃዎች*
- ❑ *የመገልገያዎች፣ የስልክ፣ የኬብል ክፍያዎች*
- ❑ *የመድን መለያ መረጃ*
- ❑ *የመኪና ክፍያ መለያ መረጃ*
- ❑ *በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ስለመኖር የሚያሳዩ መዝገቦች፡- የሊዝ መዝገቦች፣ የክፍያ ወረቀቶች፣ የትምህርት ቤት መዝገቦች፣ መግለጫዎች፣ የሂሳብ ክፍያዎች፣ ደረሰኞች፣ የሕክምና ሂሳብ ክፍያዎች፣ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ መኖሩን የሚያረጋግጡ ሌሎች ሰነዶች*
- ❑ *የወንጀል እና የኢሚግሬሽን መዝገቦች ያለ ከሆነ*
- ❑ *በአሜሪካ ውስጥ ለሁሉም ዓመታት ለቀረቡ ግብሮች የአሜሪካ የግብር መዝገቦች*
- ❑ *ደብዳቤ (በአሜሪካ ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንደኖሩ ለማረጋገጥ)*
- ❑ *ዜጋ ያልሆነ ሰው ብዛት*

---

**አስፈላጊ፡-** ወቅታዊ እንዲሆኑ እነዚህን ሰነዶች በየ 6 ወሩ ያዘምኑ።

# Section 2

# *Important Information and Contacts*

1. *የድንገተኛ ጊዜ ቡድን*

2. *ጓደኞች እና ቤተሰብ*

3. *የማህበረሰብ መርጃዎች*

4. *በአሜሪካ ውስጥ ያለ ቤተሰብ*

5. *ከአሜሪካ ውጭ ያለ ቤተሰብ*

6. *ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች መረጃ*

## 1. የድንገተኛ ጊዜ ቡድን

***የእኛ መረጃዎች፡-***

| ስም | ጎልማሳ 1፡-________________________ | ጎልማሳ 2፡- ________________________ |
|---|---|---|
| አድራሻ | | |
| የትውልድ ቦታ | | |
| የልደት ቀን | | |
| የስራ ቦታ | | |
| የስራ መርሃግብር | | |
| የሥራ ስልክ | | |
| የእጅ ስልክ | | |

## 2. የሚደወልላቸው ጓደኞች እና ቤተሰብ፡-

*ወዳጅዎ ከታሰረ በክፍል 3 ውስት ያሉ እቅዶችዎን ለመፈፀም የሚያምኗቸውን ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች ይምረጡ።*

| ስም | ስልክ ቁጥር | አድራሻ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

**3.** *የማህበረሰብ መርጃዎች፦*

| *ኤጀንሲ* | *ስም* | *ስልክ ቁጥር* |
| --- | --- | --- |
| *የICE ክስተት ሆትላይን* | CIRC | (844)864-8341 |
| *የኢሚግሬሽን ጠበቃ* | | |
| *የ ቆንስላ*___________________________ | | |
| *ቤተ ክርስቲያን፣ ቄስ፣ ፓስተር* | | |
| | | |
| | | |
| | | |

**4.** *በአሜሪካ ውስጥ ያሉ የቤተሰብ አባላት፦*

| *ስም* | *ስልክ ቁጥር* | *ዝምድና* | *አድራሻ* |
| --- | --- | --- | --- |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

**5.** ***ከአሜሪካ ውጭ ያሉ የቤተሰብ አባላት፡-***

| *ስም* | *ስልክ ቁጥር* | *ዝምድና* | *አድራሻ* |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

**6.** ***ስለ ልጆችዎ የሚመለከቱ መረጃ***

| *ሙሉ ስም* | *ልጅ፡-* ____________________ | *ልጅ፡-* ____________________ |
|---|---|---|
| *የትውልድ ቦታ እና ቀን* | | |
| *አድራሻ* | | |
| *ዜግነት* | | |
| *የህግ ሁኔታ* | | |
| *የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር (SSN)* | | |
| *ዶክተር፣ ስልክ ቁጥር* | | |
| *የጤና መድን ኩባንያ፣ ስልክ ቁጥር* | | |

| | | |
|---|---|---|
| ፖሊሲ ቁጥር | | |
| የጥርስ ሐኪም፣ ስልክ ቁጥር | | |
| የጥርስ መድን ኩባንያ፣ ስልክ ቁጥር | | |
| የሕክምና ታሪክ | | |
| የተወሰዱ መድሃኒቶች እና ድግግሞሽ | | |
| ሕጻኑ በትምህርት ቤት ውስጥ የግለሰብ የትምህርት ዕቅድ (IEP) አለው? | | |
| ሕጻኑ በአሁኑ ጊዜ በሕክምና ላይ ነው ወይ፣ በምን ምክንያት? | | |
| ቴራፒስት፣ ስልክ ቁጥር | | |
| አለርጂዎች | | |
| የትምህርት ቤት ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ | | |
| የምግዚት ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ | | |
| ክፍል | | |
| የትምህርት ቤት መርሃግብር | | |
| ወደ ትምህርት ቤት እንዴት ሄደው ይመለሳሉ? | | |

| | | |
|---|---|---|
| ከትምህርት በኋላ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አሉ? | | |
| የሚወዱት አሻንጉሊት | | |
| ሌላ | | |

***ከአራት በላይ ልጆች ካሉዎት ለመረጃቸው ይህን ገጽ ፎቶ ኮፒ ያድርጉ***

| ሙሉ ስም | ልጅ፡- | ልጅ፡- |
|---|---|---|
| የትውልድ ቦታ እና ቀን | | |
| አድራሻ | | |
| ዜግነት | | |
| የህግ ሁኔታ | | |
| የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር (SSN) | | |
| ዶክተር፣ ስልክ ቁጥር | | |
| የጤና መድን ኩባንያ፣ ስልክ ቁጥር | | |
| ፖሊሲ ቁጥር | | |
| የጥርስ ሐኪም፣ ስልክ ቁጥር | | |
| የጥርስ መድን ኩባንያ፣ ስልክ ቁጥር | | |
| የሕክምና ታሪክ | | |
| የተወሰዱ መድሃኒቶች እና ድግግሞሽ | | |
| ሕጻኑ በትምህርት ቤት ውስጥ የግለሰብ የትምህርት ዕቅድ (IEP) አለው? | | |
| ሕጻኑ በአሁኑ ጊዜ በሕክምና ላይ ነው ወይ፣ በምን ምክንያት? | | |
| ቴራፒስት፣ ስልክ ቁጥር | | |
| አለርጂዎች | | |
| የትምህርት ቤት ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ | | |

| | | |
|---|---|---|
| የምግዚት ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ | | |
| ክፍል | | |
| የትምህርት ቤት መርሃግብር | | |
| ወደ ትምህርት ቤት እንዴት ሄደው ይመለሳሉ? | | |
| ከትምህርት በኋላ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አሉ? | | |
| የሚወዱት አሻንጉሊት | | |
| ሌላ | | |

# ክፍል 3
# *የቤተሰብ እቅዶች*

1. *ለልጆች*

2. *ባል፣ ሚስት ወይም አጋር ከተወሰደ*

3. *ሁለቱም ወላጆች ከተወሰዱ*

4. *ቤት፣ አፓርታማ፣ ተጎታች*

5. *መኪና፣ የጭነት መኪና*

6. *የመገልገያ ሂሳቦች*

7. *የቤት ዕቃዎች እና ሌሎች ንብረቶች*

8. *ህጋዊ እርምጃ*

9. *ሌሎች መመሪያዎች*

1. ***ለልጆቻችን ያለን እቅዳችን***

****** ልጆቻችሁን ለሚተዉላቸው ሰዎች ጥቢቃ የአሜሪካ ዜጎች ወይም ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪዎች ቢሆኑ የተሻለ ነው። እንዲሁም፣ የልጆቻችሁ ተንከባካቢ አድርጋችሁ የምትመድቡዋቸው ሰዎች በመመደባቸው የሚስማሙ መሆን አለባቸው።******

*እኛ እዚህ የማንኖር እና ልጆቻችንን ለመንከባከብ የማንገኝ ከሆነ፣ ልጆቻችን በሚከተሉት እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ፍላጎታችን ነው፡-*

*ስሞች* ______________________________

*አድራሻ* ______________________________

*ስልክ(ኮች)* ______________________________

*ዜግነት* ______________________________

*መመሪያዎች፡-*

______________________________

______________________________

______________________________

*የተሰየመው ሰው(ዎች) ልጆቻችንን መንከባከብ ካልቻሉ ደግሞ ሁለተኛ ምርጫ፡-*

*ስሞች* ______________________________

*አድራሻ* ______________________________

*ስልክ(ኮች)* ______________________________

*ዜግነት* ______________________________

*መመሪያዎች፡-*

______________________________

______________________________

______________________________

**2. *አንድ የትዳር አጋር ከታሰረ ያለዎት ዕቅድዎ፡-***

*መመሪያዎች፡-*

___

___

___

**3. *ሁለቱም ወላጆች ከታሰሩ የእርስዎ ዕቅድ፡-***

*መመሪያዎች፡-*

___

___

___

**4. *ለቤታችን፣ ለአፓርታማችን፣ ለተጎታች መኪናችን ያለን ዕቅዳችን፡-***

*ኪራይ፣ ሞርጌጅ፣ የተጎታች ኩባንያ*

___

*አድራሻ* ___

*ስልክ* ___

*ወርሃ ክፍያ መጠን* ___ *የክፍያ ቀን* ___

*መመሪያዎች፡-*

___

___

___

**5. *ለተሽከርካሪያችን ያለን እቅዳችን***

*መመሪያዎች፡-*

___

___

___

| ስሪት | ሞዴል | ዓመተ ምህረት | የአሁኑ ዋጋ |
| --- | --- | --- | --- |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

6. ***የመገልገያዎች (ሂሳብ ክፍያዎች) እቅድ፡-***

*ከዚህ በታች ያሉትን የመገልገያ ክፍያዎች ስለመክፈል መመሪያዎች፡-*

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

| *ሂሳብ*<br>*ወርሃዊ መጠን* | *ስልክ ቁጥር* | *አድራሻ* |
| --- | --- | --- |
| *የባንክ መረጃ*<br>$ ________________ | | |
| *ሞርጌጅ፣ የቤት ኪራይ፣ የመለያ መረጃ*<br>$ ________________ | | |
| *የኤሌክትሪክ መለያ መረጃ*<br>$ ________________ | | |
| *የስልክ መለያ መረጃ*<br>$ ________________ | | |
| *የኬብል፣ የሳተላይት መለያ መረጃ*<br>$ ________________ | | |
| *የመድን መለያ መረጃ*<br>$ ________________ | | |

| የመኪና ክፍያ መለያ መረጃ<br>$ ________________ | | |
| --- | --- | --- |

7. **ለቤት ኢቃዎቻችን እና ንብረቶቻችን ያለን እቅዳችን፦**

*መመሪያዎች፦*

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

8. **ህጋዊ እቅድ**

**A.** ***የታሰርኩ ጠበቃ ለማነጋገር ፍላጎቴ ነው፦***

ጠበቃ ________________________________________

አድራሻ________________________________________

ስልክ________________________________________

**B.** ***ሁለተኛ ምርጫ ጠበቃ፦***

ጠበቃ ________________________________________

አድራሻ________________________________________

ስልክ________________________________________

*የጠበቃ መመሪያዎች፦*

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

**C. *የኢሚግሬሽን ዳራዬ ማጠቃለያ፡-***

| | | |
|---|---|---|
| | | |
| A#፣ (ከሌለዎት "የለም" ብለው ይጻፉ) | | |
| አሜሪካ ገቡት በቪዛ ነበር? | አዎ ካሉ፣ የቪዛው አይነት___________ | አዎ ካሉ፣ የቪዛው አይነት___________ |
| ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አሜሪካ የገቡበት ቀን | | |
| የወጡበት እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወደ አሜሪካ የገቡባቸው ቀናት፡- | ከ __/__/__ - እስከ __/__/__ | ከ __/__/__ - እስከ __/__/__ |
| ወደ አሜሪካ የተመለሱት በምርመራ ወይም በፍቃድ ነው? መቼ? | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ |
| ወደ አሜሪካ የገቡበት ከተማ | | |
| በኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ሂደቶች ላይ ተሳትፈዋል? | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ |
| ከዚህ በፊት በአሜሪካ ድንበር ላይ ቁጥጥር ስር ውለው ነበር? | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ |
| ከኤፕሪል 30 ቀን 2001 በፊት "የውጭ ዜጋ ዝምድና ፒያቄ" ያቀረበልዎት ሰው አለ? | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ |
| ከ 30 ኤፕሪል 2001 በፊት "የሰራተኛ ማረጋገጫ" ያቀረበልዎት ሰው ነበር? | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ | አዎ ካሉ፣ መቼ? ___/___/___ |

| | | |
|---|---|---|
| *በአሁኑ ጊዜ ከአገር ለመባረር ሂደቶች ላይ ነዎት?* | | |
| *ከአገር ተባረዋል?* | *እባክዎን ያብራሩ፡-* | *እባክዎን ያብራሩ፡-* |
| *DACA አለዎት?* | | |

**D.** ***የአሜሪካ ቤተሰቤ ዝምድናዎች ማጠቃለያ፡-***

---

*በሕጋዊ መንገድ አግብተዋል?* *አዎ ካሉ፣ መቼ?*____/____/____

*አይ፡-*________

*በቤተክርስቲያን አግብተዋል?* *አዎ ካሉ፣ መቼ?*____/____/____

*አይ፡-*________

*የባለቤቴ ወይም የትዳር አጋሬ ዜግነት*________________________________________

*የነዋሪነት ሁኔታ*______________________________________________

*የባለቤቴ ወይም የትዳር አጋሬ ዜግነት*________________________________________

*የነዋሪነት ሁኔታ*______________________________________________

**E.** ***የአሜሪካ ዜጎች ወይም ህጋዊ ቋሚ ነዋሪዎች የሆኑ ሌሎች ዘመዶቼ፡-***

| *ስም* | *ዝምድና* | *ዜግነት* | *አድራሻ* |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |

## F. ሌሎች አጠቃላይ መመሪያዎች፡-

*መመሪያዎች፡-*

# Section 4
# *Identification & Documents*

1. *የውክልና ቅጾችን በተመለከተ አስፈላጊ ማስታወሻዎች*
2. *የውክልና ስልጣን ማስጠንቀቂያ እና ግልጽ ተጠያቂነትን መተው*
3. *የውክልና ቅጾች*
    a. *ዓላማው የተወሰነ ውክልና መመሪያዎች*
    b. *ዓላማው የተወሰነ ውክልና*
    c. *በወላጅ ወይም በአሳዳጊ የሚሰጥ የውክልና ስልጣን መመሪያዎች*
    d. *በወላጅ ወይም በአሳዳጊ የሚሰጥ የውክልና ስልጣን*

*የሚከተሉትን በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰነዶችን ያስቀምጡ እና ሲካተቱ ሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ፡-*

- ❑ *የምስክር ወረቀቶች (ዋና እና ፎቶ ኮፒዎች)*
- ❑ *መታወቂያ (የኮሎራዶ መንጃ ፈቃድ ፎቶ ኮፒዎች፣ ሌሎች መታወቂያዎች)*
- ❑ *የክትባት መዝገብ (ዋናው እና ፎቶ ኮፒ)*
- ❑ *የቤተሰብ ፎቶዎች*
- ❑ *የውክልና ስልጣን*

## *የውክልና ቅጾችን በተመለከተ አስፈላጊ ማስታወሻዎች*

1. *ሙሉ በሙሉ የሚያምኑትን ሰው ብቻ “እንደራሴ” አድርገው መምረጡ በጣም አስፈላጊ ነው። እርስዎ በማይኖሩበት ጊዜ በእነዚህ ቅጾች የተሰጠውን ስልጣን አላግባብ ሊጠቀም የሚችል ሰውን "እንደራሴ" እንድሆንዎት አይምረጡ።*

2. *የውክልና ስልጣን ቅጾችን ከመሙላትዎ በፊት "እንደራሴ" አድርገው ከሚሰይሙት ሰው ፈቃድ ያግኙ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እርስዎ በማይኖሩበት ጊዜ ግለሰቡ እርስዎን ወክሎ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለብዎት።*

3. *በእነዚህ ቅጾች ስለሚፈቀዱ ስልጣኖች ልዩ የሕግ ምክር ለማግኘት በኮሎራዶ ስቴት ባር ፈቃድ ያለውን ጠበቃ ያማክሩ። የውክልና ስልጣን ቅጾችን ለማረጋገጥ ከአነስተኛ ክፍያ በላይ የሚያስከፍል ማንኛውንም "ሰነድ አረጋጋጭ" መጠራጠር አለብዎት። ለግል ሁኔታዎ ልዩ የሆነ ዝርዝር የውክልና ስልጣን ቅጽ ለማዘጋጀት ፍላጎት ካለዎት፣ በኮሎራዶ ስቴት ባር ፈቃድ ያለውን ጠበቃ ያማክሩ። ባለቤትነቱ የእርስዎ ለሆነ ቋሚ ንብረት የውክልና ስልጣን ለማዘጋጀት የሚፈልጉ ከሆነ፣ በኮሎራዶ ስቴት ባር ፈቃድ ያለውን ጠበቃ ያማክሩ።*

**ማስታወሻ፡-***ፈቃድ ለሌለው ጠበቃ ወይም እውቅና ያለው ለትርፍ ያልተቋቋመ ኤጀንሲ ሰራተኛ ሰው የኢሚግሬሽን ድጋፍ ገንዘብ በጭራሽ አይክፈሉ። ለሕዝብ የኢሚግሬሽን ድጋፍ እንሰጣለን በሚሉ “ሀሰተኛ የህግ አማካሪዎች” ብዙ ሰዎች በህግ እና በገንዘብ ተጎድተዋል።*

**ማስታወሻ፡-***በአሁኑ ጊዜ የኢሚግሬሽን ጠበቃ ካለዎት፣ የሚታሰሩበትን ክስተት በተመለከተ ከጠበቃዎ ጋር እቅድ ያዘጋጁ። ለዋስትና ማመልከት ከፈለጉ ወይም ሌሎች ማመልከቻዎችን ለ ICE ወይም ለኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ማስገባት ካለብዎት ለህጋዊ ውክልና ምን ያህል ክፍያ እንደሚያስከፍል ጠበቃውን ይጠይቁ።*

****_**እነዚህ መመሪያዎች የሕግ ምክር አይደሉም። በእነዚህ ቅጾች ስለሚፈቀዱ ስልጣኖች ልዩ የሕግ ምክር ለማግኘት በኮሎራዶ ስቴት ባር ፈቃድ ያለውን ጠበቃ ያማክሩ።**_ ****

**የውክልና ስልጣን -ማስጠንቀቂያ እና ግልጽ ተጠያቂነትን መተው**

እባክዎን ይህንን ሰነድ በጥንቃቄ ያንብቡ።

ቅጽ JDF 751 ወይም አጠቃላይ ዓላማው የተወሰነ -የውክልና ስልጣን ቅጽ ማቅረብ እና ማብራራትን የሚያካትት ማንኛውም በኮሎራዶ የስደተኞች መብቶች ጥምረት የሚሰጥ ድጋፍ በእርስዎ እና በኮሎራዶ የስደተኞች መብቶች ጥምረት መካከል የጠበቃ/የደንበኛ ግንኙነት እንደማይፈጥር ይረዳሉ።

ዓላማው የተወሰነ ሕጋዊ ውክልና ስልጣን የሚሰጡት ሰው እምነት የሚጣልበት ግለሰብ መሆኑን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ካልሆኑ በስተቀር ቅጽ JDF 751 ወይም አጠቃላይ ዓላማው የተወሰነ -የውክልና ስልጣን ቅጽ መፈረም እንደሌለበት ይረዳሉ። እርስዎ በሌሉበት ጊዜ ለልጆችዎ ወይም ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች እንዲወስን ሥልጣን እንደምትሰጡት፣ እና ውሳኔውን በጥንቃቄ መመርመር እንዳለብዎት ይረዳሉ። እንዲሁም ያንን ስልጣን በጽሑፍ በማንኛውም ጊዜ መሻር እንደሚችሉ ይረዳሉ።

ቅጽ JDF 751 ወይም አጠቃላይ ዓላማው የተወሰነ -የውክልና ስልጣን ቅጽን በማንኛውም የኮሎራዶ የስደተኞች መብቶች ጥምረት ጽ/ቤት ውስጥ፣ ፓኬት ውስጥ ወይም ስፖንሰር በተደረገ ዝግጅት ላይ ከፈረሙ፣ ይህንን ያደረጉት በራስዎ ፈቃድ መሆኑን ይገነዘባሉ። እርስዎ እንዲፈርሙ ያልተገደዱ ወይም ማስፈራሪያ አልተደረገብዎት ሲሆን፣ ስለ ሁለቱም ቅጽ የሕግ ምክር እንዳልተሰጡዎት ይስማማሉ። የውክልና ስልጣን ኃላፊነቶች የአጭር እና የረዥም ጊዜ ውጤቶችን በተመለከተ ነፃ የህግ አማካሪ እና ትንታኔ እንዲፈልጉ በግልፅ ይመከራሉ።

የኮሎራዶ የስደተኞች መብቶች ጥምረት በማንኛውም የኮሎራዶ የስደተኞች መብቶች ጥምረት ጽ/ቤት ውስጥ፣ ፓኬት ውስጥ ወይም ስፖንሰር በተደረገ ዝግጅት ላይ የተቀበሉትን ማንኛውንም የውክልና ስልጣን ቅጾችን ለመጠቀም ወይም ለማስፈፀም በመምረጥዎ ምንም ዓይነት ኃላፊነት እንደሌለው ይስማማሉ።

<u>ዓላማው የተወሰነ የውክልና ስልጣን መመሪያዎች</u>

**"ዓላማው የተወሰነ"** የውክልና ስልጣን ቅጽ አንድ ሰው ውሳኔዎችን እንዲያደርግ እና በገንዘብ ጉዳዮች ላይ እርስዎን ወክሎ እንዲሠራ ሊፈቅድልዎት የሚስል ሲሆን እርስዎ የሚፈልጉትን ያህል የበዛ ወይም ያነሰ ስልጣን ሊሰጡ ይችላሉ። ከሚከተሉት ውስጥ ጥቂቶቹን ወይም ሁሉንም እንዲያደርግ ለወኪልዎ ስልጣን ለመስጠት ሊያስቡ ይችላሉ፡-

- የዕለት ተዕለት ወጪዎችዎን እና የቤተሰብዎን ወጪዎች ለመክፈል ንብረቶችዎን እንዲጠቀሙ
- የማይንቀሳቀስ ንብረት እና ሌሎች ንብረቶችን እንዲገዙ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲጠግኑ፣ ግብር እንዲከፍሉ እና ማስያዣ እንዲያደርጉ
- ማህበራዊ ዋስትና፣ ሜዲኬር ወይም ሌሎች የመንግስት ጥቅማጥቅሞችን እንዲሰበስቡ
- በአክሲዮን፣ በቦንድ እና በጋራ ፈንድ ውስጥ ያለው ገንዘብዎን ኢንቨስት እንዲያደርጉ
- ከባንኮች እና ከሌሎች የገንዘብ ተቋማት ጋር ያለውን ግብይቶች እንዲያከናውኑ
- የመድን ፖሊሲዎችን እና የፋይናንስ ኮንትራቶችን ለእርስዎ እንዲገዙ እና እንዲሸጡ
- የግብር ክፍያዎችን እንዲያዘጋጁ እና እንዲከፍሉልዎት
- አነስተኛ ንግድዎን እንዲያንቀሳቅሱ
- እርስዎ የሚወርሱትን ወይም በሌላ መንገድ ለመጠቀም መብት ያለዎትን ንብረት እንዲጠይቁ
- ቀደም ሲል ለፈጠሩት ትረስት ንብረት እንዲያስተላልፉ
- በፍርድ ቤት እርስዎን የሚወክል ሰው እንዲቀጥሩ፣ እና
- የጡረታ ሂሳቦችዎን እንዲቆጣጠሩ።

ወኪሉ ለእርስዎ ጥቅም እንዲሠራ፣ ትክክለኛ መዝገቦችን እንዲይዙ እና ንብረታቸውን ከእርስዎ እንዲለዩ ይጠበቅባቸዋል። ይህ ስልጣን ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ መምረጥ ይችላሉ። ምርጫ (ሐ) (በገጽ 2 ላይ) ለአብዛኞቹ ሰዎች በጣም ተግባራዊ ምርጫ ይሆናል።

የውክልና ስልጣኑ መነሳት እንስከሚያስፈልገው ድረስ የቅጹ ገጽ 3 ጥቅም ላይ አይውልም። በዚያ ጊዜ፣ ወኪሉ እርስዎን ወክሎ እርምጃ ለመውሰድ ሲሞክር ገጽ ሶስት ሞልቶ ሰነዱን ያቀርባል።

ፍቺዎች፡-

1. ዋና፡- እርስዎ- ለሌላ ሰው ውሳኔዎችን በራሱ/ሷ እንዲወስኑ ስልጣን የሚሰጥ ሰው
2. ወኪል፡- እርስዎን በመወከል ውሳኔ እንዲወስን የሚመርጡት ሰው
3. ስልጣን መስጠት- እርስዎ፣ ዋናው፣ እርስዎ ለፈቀዱት ስልጣን እርስዎ እንዳሉ ሆኖ እንዲያገለግል ለወኪልዎ መብት እየሰጡ ነው፡- ማለትም፣ ከላይ ያለውን ዝርዝር ይመልከቱ፣ የተዘረዘሩት ስልጣናት ብቻ ለወኪሉ እንደተሰጡ ስልጣን ይወሰዳሉ።
4. ወኪሉ የዋናውሰው የትዳር ኢጋር፣ ወላጅ ወይም ልጅ ካልሆነ በስተቀር ወኪሉ እራሱን ወይም እዳ ያለበትን ሌላ ሰው እንዲጠቅም አይፈቀድለትም።

# የውክልና ስልጣን
# (ዓላማው የተወሰነ)

| |
|---|
| **አስፈላጊ መረጃ**<br><br>ይህ የውክልና ስልጣን ሌላ ሰው (ወኪልዎ) ለእርስዎ (ዋናው) ውሳኔ እንዲወስን እና በተሰጠ ስልጣን ውስጥ ከዚህ በታች የተገለጸውን ውስን ዓላማ በተመለከተ እርስዎን ወክሎ እንዲሠራ ይፈቅድለታል። የእርስዎ ወኪል ሆነው እንዲያገለግሉ የሚያምኑትን ሰው መምረጥ አለብዎት። እርስዎ በሌላ መንገድ ካልገለጹ በስተቀር፣ በአጠቃላይ የወኪሉ ስልጣን እርስዎ እስኪሞቱ ወይም የውክልና ስልጣኑን እስኪሽሩ ድረስ ወይም ተወካዩ ስራውን እስከሚለቅ ድረስ ወይም ለእርስዎ መስራት እስካልቻለ ድረስ ይቀጥላል።<br>በልዩ መመሪያዎች ውስጥ ካልገለጹት በስተቀር ወኪልዎ ተመጣጣኝ ካሳ የማግኘት መብት አለው።<br><br>**ይህ የውክልና ስልጣን ወኪሉ የጤና እንክብካቤ ውሳኔዎችን ለእርስዎ እንዲሰን አይፈቅድም። ይህን የውክልና ስልጣን ወይም ለወኪልዎ ስለሚሰጡት ስልጣን ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ይህን ቅጽ ከመፈረምዎ በፊት የሕግ ምክር መፈለግ አለብዎት።** |

**የወኪል ስያሜ**

እኔ፣ ________________________ (የዋና ስም)፣ የሚከተለውን ሰው እንደ ወኪሌ እሰይማለሁ፡-

የወኪል ስም፡- ________________________________

የወኪል አድራሻ፡- ________________________________

የወኪል ስልክ ቁጥር፡-________________________________

**ሥልጣን መስጠት**

የሚከተለውን ድርጊት ወይም ግብይት ለመፈፀም እና ለማጠናቀቅ እኔ በግሌ ብገኝ እንደማደርገው ሁሉ ወኪሌ እንደራሴ እና ህጋዊ ወኪል ሆኖ ሁሉንም አስፈላጊ ድርጊቶች በስሜ፣ በቦታዬ ሆኖ እንዲሁም ወክሎኝ ለብቻዬ ፋይዳ እና ጥቅም በሙሉ ስልጣን እንዲሠራ ስልጣን እሰጣለሁ። *(ድርጊቱን ወይም ግብይቱን ለማከናወን የተፈቀዱ ልዩ ኃላፊነቶች እና ገደቦችን ጨምሮ ድርጊቱን ወይም ግብይቱን በዝርዝር ይግለጹ።)*

**በወኪል ስልጣን ላይ ያለ ገደብ**

የእኔ ቅድመ አያት፣ የትዳር አጋር ወይም ዘር ያልሆነ ወኪል ይህንን የውክልና ስልጣን ለራሳቸው ጥቅም ወይም የድጋፍ ግዴታ ላለባቸው ለማንም ሰው ጥቅም እንዳይውል የተከለከለ ነው። በዚህ የውክልና ሥልጣን የተሰጠው ሥልጣን በዚህ ሰነድ በተገለጸው ድርጊት ወይም ግብይት የተገደበ ነው።

**ልዩ መመሪያዎች**

በሚከተሉት መስመሮች ላይ ልዩ መመሪያዎችን መስጠት ይችላሉ፡-

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**የሚጸናበት ቀን እና ማቋረጥ**

*መመሪያዎች፡- (ሀ) ወይም (ለ)ን በማስጀመር የዚህን የውክልና ስልጣን የሚፀናበትን ቀን ይምረጡ። ሁለቱም ካልተጀመሩ፣ ይህ የውክልና ስልጣን ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናል። ይህ የውክልና ስልጣን ዓላማውን ሲያጠናቅቅ፣ በእርስዎ በኩል ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስዱ ወዲያውኑ እንዲያበቃ ከፈለጉ፣ የመጀመሪያ (ሐ)ን ያስጀምሩ።*

(A) ይህ የውክልና ስልጣን ወዲያውኑ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን ወደፊት በእኔ በኩል እክል ቢኖረኝም ተፈጻሚነቱን ይቀጥላል።

(B) ይህ የውክልና ስልጣን ወደፊት እክል ሲገጥመኝ ተፈጻሚ ይሆናል።

(C) ይህ የውክልና ስልጣን በዚህ ውስጥ የተቀመጠውን ውስን ዓላማ ሲያጠናቅቅ ወዲያውኑ ተፈጻሚነቱ ያበቃል።

**በዚህ የውክልና ስልጣን ላይ መተማመን**

(1) በሙሉ የመሻር ስልጣን፣ በዚህ የውክልና ስልጣን እና በዚህ ውስጥ ባለው ስልጣን ምክንያት ወኪሌ በሕጋዊ መንገድ የሚያደርገውን ወይም እንዲፈጸም የሚያደርገውን ሁሉ በማጽደቅ አረጋግጣለሁ። ወኪሌን ጨምሮ ማንኛውም ሰው በዚህ የውክልና ስልጣን ትክክለኛነት ወይም ያ ሰው እንደተቋረጠ ወይም ዋጋ እንደሌለው ካላወቀ በስተቀር በዚህ የውክልና ቅጂ ሊተማመን ይችላል።

**ፊርማ እና እውቅና**

______________________________
ቀን

______________________________
የዋና ፊርማ
ስምዎን ይጻፉ፡- ______________________________
አድራሻ፡- ______________________________
______________________________
የእርስዎ ስልክ ቁጥር፡- ______________________________

የ ስቴት ______________________________
የ ካውንቲ ______________________________

ይህ የውክልና ስልጣን በፊቴ እውቅና ያገኘው በ ______________________________ (ቀን)፣ በ ______________________________ ነው። (የዋናው ስም)

______________________________
የሰነድ አረጋጋጭ ፊርማ
የእኔ ኮሚሽን የሚያበቃው፡- ______________________________

**የወኪል የውክልና ስልጣን ትክክለኛነት**
**እና የተፈቀዱ ስልጣኖቻቸው ማረጋገጫ**

የ ስቴት ________________________

የ ካውንቲ ________________________

I, ________________________ (Name of Agent), certify under penalty of perjury that
________________________ እንደ ወኪል ወይም እንደ ተተኪ ወኪል
የውክልና ስልጣን የሰጠኝ (ዋና ስም) ቀን ________________________ ።

ይህንንም በእኔ እውቀት አረጋግጣለሁ፡-

(1) ዋናው በሕይወት ያለ ሲሆን የውክልና ሥልጣኑን ወይም በውክልና ስልጣኑ መሰረት ያለኝን ስልጣን አልሻረውም እናም የውክልና ስልጣኑ እና በውክልና ስልጣኑ መሰረት ያለኝ ስልጣኔ አልተቋረጠም፤

(2) የውክልና ስልጣኑ የተነደፈው ክስተት ወይም ድንገተኛ ሁኔታ ሲከሰት ተፈጻሚ እንዲሆን ከሆነ፣ ክስተቱ ወይም ድንገተኛ ሁኔታው ተከስቷል፤

(3) እኔ እንደ ተተኪ ወኪል ከተሰየምኩኝ፣ ቀዳሚው ወኪል ከአሁን በኋላ ለማገልገል አይችልም ወይም ፈቃደኛ አይደለም፤ እና

(4) ________________________
(ሌሎች ተዛማጅ መግለጫዎችን ያስገቡ)

**ፊርማ እና እውቅና**

________________
ቀን

________________________
የወኪል ፊርማ
የወኪል የተጻፈ ስም፡- ________________________
የወኪል አድራሻ፡- ________________________
________________________
የወኪል ስልክ ቁጥር፡- ________________________

ይህ ሰነድ በ ________________________ (ቀን) ከእኔ ፊት
በሚከተለው አካል እውቅና አግኝቶ ነበር
________________________. (የወኪል ስም)

________________________
የሰነድ አረጋጋጭ ፊርማ
የእኔ ኮሚሽን የሚያበቃው፡- ________________________

## በወላጅ ወይም በአሳዳጊ የሚሰጥ የውክልና ስልጣን JDF 751
## ለመሙላት የሚረዱ መመሪያዎች:-

ቅጽ JDF 751 በቅጹ ላይ ከተገለጹት ልጆች ጋር በተያያዘ ለተሰየመው ሰው የአሳዳጊነት ግንኙነት አይፈጥርም። የተሾመው ሰው ጋብቻን ወይም ጉዲፈቻን የመፍቀድ ሥልጣን ካልሆነ በስተቀር ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ እንክብካቤን፣ ጥበቃን ወይም ንብረትን በሚመለከት ለማንኛውም ሥልጣን ከአሥራ ሁለት ወራት ላልበለጠ ጊዜ የተገደበ ሥልጣን ይኖረዋል። ስልጣኑ ሊታደስ ወይም ሊሻር ይችላል። ቅጽ JDF 751 ሲፈረም ተፈጻሚ ይሆናል። ስለሆነም ሊፈረም ይችላል ነገር ግን አስፈላጊ እስከሚሆን ድረስ ቀን ላይጻፍበት እና ለተሰየመው ሰው ላይሰጥ ይችላል።

1. በቅጹ አናት ላይ ባለው በ1ኛው ባዶ ቦታ (ሙሉ ስም) በሚልበት ላይ እባክዎን የወላጅ ወይም የአሳዳጊውን ስም ያስገቡ።

2. የልጁን ስም ወይም "አቅም የሌለው ሰው" ስም በሚጠይቅበት ቦታ ላይ የልጆቹን ወይም ለራሳቸው ጤና፣ ደህንነት መንከባከብ ወይም የግላቸውን እንክብካቤ ማድረግ ስለማይችሉ መረጃ መቀበል ወይም መገምገም የማይችሉ ሌላ ማንኛውም ሰው ስም ያስቀምጡ። (ይህ ልጆች፣ አረጋውያን ዘመዶች፣ አካል ጉዳተኛ የቤተሰብ አባላት፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ።) <u>ስሞቹን የዚያ ሰው የልደት የምስክር ወረቀት ላይ እንደተጻፉት መጽሃፍዎን ያረጋግጡ እና ያስቀምጡ፣</u>

3. የእያንዳንዱን ልጅ ወይም አቅም የሌለው ሰው የልደት ቀን ያካትቱ።

4. "ዝምድና" የሚልበት ቦታ ላይ ልጁ "ባዮሎጂካል" ልጅ ወይም "የማደጎ ልጅ" መሆኑን ያስቀምጡ

5. "የሰውየው ስም" በሚጠይቅበት ቦታ ላይ አንድ ሰው በልጁ ወይም አቅም በሌለው ሰው መብቶች ላይ እርስዎን ወክሎ እንዲሠራ የተፈቀደለትን <u>አንድ ሰው</u> ስም ይጻፉ።

6. ከገጹ ግርጌ ላይ "ይህ ልዩ የውክልና ስልጣን እስከ ___________ የሚፀና ይሆናል" በሚልበት ቦታ ላይ ይህ ፈቃድ እንዲያበቃበት የሚፈልጉትን ቀን ያስቀምጡ። ይህንን ቅጽ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ብቻ መፍቀድ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ይህ የተፈረመበት ቀን 12/31/17 ከሆነ፣ ይህንን ቅጽ እስከ 12/31/18 ድረስ ብቻ ተፈጻሚ እንዲህን ማድረግ ይችላሉ።

7. ወላጅ ወይም አሳዳጊ ቀን በመጻፍ በቅጹ ገጽ ግርጌ ላይ ፈርሙ።

# በወላጅ ወይም በአሳዳጊ
# በ15-14-105, C.R.S መሰረት የሚሰጥ የውክልና ስልጣን

እኔ ______________________________ ፣(ሙሉ ስም)፣ ከታች የተጠቀሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ(ልጆች) ወይም አቅም የሌለው ሰው(ዎች) ወላጅ ወይም አሳዳጊ፡-

| የልጁ ወይም አቅም የሌለው ሰው ሙሉ ስም | የልደት ቀን | ዝምድና |
|---|---|---|
| | | |

(የሰው ስም) በኔ ቦታ እንደራሴ ሆኖ በሙሉ ሥልጣን እንደሚከተለው እንዲሠራ እሾማለሁ፡-

1. በ§15-14-105, C.R.S. ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ መልኩ ከላይ ለተጠቀሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወይም አቅም የሌለው ሰው ለዕለት ተዕለት እንክብካቤ፣ ጥበቃ፣ ትምህርት፣ መዝናኛ እና ንብረት አስፈላጊ የሆኑትን ማንኛውንም እና ሁሉንም ተግባራት እንዲያከናውኑ።

2. ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጅ(ጆች) ወይም አቅም ለሌለው ሰው(ዎች) ጤና እና ደህንነት ማንኛውንም እና ሁሉንም የሕክምና እንዲሁም የጥርስ እንክብካቤን እንዲፈቅዱ። ይህ እንክብካቤ እነዚህን ያካትታል ነገር ግን በእነዚህ አይገደብም፣ የሕክምና እና የጥርስ ምርመራዎች፣ ኤክስሬይ፣ ለቀዶ ጥገናዎች፣ ማደንዘዣ መድሃኒት እና የሆስፒታል እንክብካቤ ናቸው።

ይህ ልዩ የውክልና ስልጣን ለእንደራሴው ለልጁ ወይም አቅም ለሌለው ሰው ጋብቻ ወይም ጉዲፈቻ ፈቃድ እንዲሰጥ ስልጣን አይሰጥም።

ይህ ልዩ የውክልና ስልጣን ቀድሞ በወላጅ ወይም በአሳዳጊ በጽሑፍ እስካልተሻረ ድረስ እስከ __________ ድረስ ተፈጻሚ ይሆናል። በማንኛውም ሁኔታ፣ በዚህ ውስጥ የተሰጠው ስልጣን በዚህ ሰነድ ከተጻፈው ቀን ጀምሮ ከ 12 ወራት በላይ አይሠራም።

ቀን፡- ______________________ ______________________________

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ

---

በ ካውንቲ፣
በ ____________________ ስቴት፣ በ ____________ ቀን ________________ 20 ______ በፊቴ ተመዝግቦ ተረጋግጦዋል፣ ወይም መሃላ ተደርጓል።

የእኔ ኮሚሽን ጊዜው የሚያበቃው፡- ______________ ______________________________

የህዝብ ሰነድ አረጋጋጭ/ጸሐፊ

**በወላጅ ወይም በአሳዳጊ**
**በ15-14-105, C.R.S መሰረት የሚሰጥ የውክልና ስልጣን**

እኔ፣ ______________________________ (ሙሉ ስም)፣ ከታች የተጠቀሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ(ልጆች) ወይም አቅም የሌለው ሰው(ዎች) ወላጅ ወይም አሳዳጊ፡-

| የልጁ ወይም አቅም የሌለው ሰው ሙሉ ስም | የልደት ቀን | ዝምድና |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

(የሰው ስም) በኔ ቦታ እንደራሴ ሆኖ በሙሉ ሥልጣን እንደሚከተለው እንዲሠራ እሾማለሁ፡-

1. በ§15-14-105, C.R.S. ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ መልኩ ከላይ ለተጠቀሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ(ጆች) ወይም አቅም የሌለው ሰው(ዎች) ለዕለት ተዕለት እንክብካቤ፣ ጥበቃ፣ ትምህርት፣ መዝናኛ እና ንብረት አስፈላጊ የሆኑትን ማንኛውንም እና ሁሉንም ተግባራት እንዲያከናውኑ።

2. ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጅ(ጆች) ወይም አቅም ለሌለው ሰው(ዎች) ጤና እና ደህንነት ማንኛውንም እና ሁሉንም የሕክምና እንዲሁም የጥርስ እንክብካቤን እንዲፈቅዱ። ይህ እንክብካቤ እነዚህን ያካትታል ነገር ግን በእነዚህ አይገደብም፣ የሕክምና እና የጥርስ ምርመራዎች፣ ኤክስሬይ፣ ለቀዶ ጥገናዎች፣ ማደንዘዣ መድሃኒት እና የሆስፒታል እንክብካቤ ናቸው።

ይህ ልዩ የውክልና ስልጣን ለእንደራሴው ለልጁ(ጆቹ) ወይም አቅም ለሌለው ሰው(ዎች) ጋብቻ ወይም ጉዲፈቻ ፈቃድ እንዲሰጥ ስልጣን አይሰጥም።

ይህ ልዩ የውክልና ስልጣን ቀድሞ በወላጅ ወይም በአሳዳጊ በጽሑፍ እስካልተሻረ ድረስ እስከ _____ ድረስ ተፈጻሚ ይሆናል። በማንኛውም ሁኔታ፣ በዚህ ውስጥ የተሰጠው ስልጣን በዚህ ሰነድ ከተጻፈው ቀን ጀምሮ ከ 12 ወራት በላይ አይሠራም።

ቀን፡- ____________________ ______________________________________

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ

በ ካውንቲ፣ በ ስቴት፣ በዚህ ቀን 20 በፊቴ ተመዝግቦ ተረጋግጦዋል፣ ወይም መሃላ ተደርጓል።

በ ካውንቲ፣
በ ______________________ ስቴት፣ በ ____________ ቀን ________________ 20 _____ በፊቴ ተመዝግቦ ተረጋግጦዋል፣ ወይም መሃላ ተደርጓል።

የእኔ ኮሚሽን ጊዜው የሚያበቃው፡- ______________ ______________________________________

የህዝብ ሰነድ አረጋጋጭ/ጸሐፊ

# ክፍል 5
# *ሌሎች የግል ሰነዶች*

*የሚከተሉትን በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰነዶችን ያስቀምጡ እና ሲካተቱ ሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ፡-*

- ❑ *በአሜሪካ ውስጥ ስለመኖር የሚያሳዩ መዝገቦች*
- ❑ *የሊዝ መዝገቦች*
- ❑ *የክፍያ ወረቀቶች*
- ❑ *የትምህርት ቤት መዝገቦች*
- ❑ *መግለጫዎች፣ ሂሳቦች፣ ደረሰኞች*
- ❑ *የሕክምና ሂሳቦች*
- ❑ *አሜሪካ ከገቡበት ቀን ጀምሮ አሜሪካ ውስጥ ስለመኖር የሚያሳዩ ሌሎች ቀን የተጻፈባቸው ሰነዶች*
- ❑ *የኢሚግሬሽን መዝገቦች (የሚመለከተው/የሚገኝ ከሆነ)*
- ❑ *የኢሚግሬሽን ማመልከቻዎች፣ የፍርድ ቤት ሂደቶች፣ የICE ሂደቶች*
- ❑ *የአሜሪካ የወንጀል መዝገቦች (የሚመለከተው/የሚገኝ ከሆነ)*
- ❑ በየወንጀሉ ስለተፈረደ ፈርድ የተረጋገጠ መዝገብ
- ❑ *በአሜሪካ ውስጥ ለሁሉም ዓመታት ለቀረቡ ግብሮች የአሜሪካ የግብር መዝገቦች*
- ❑ *ደብዳቤዎች*

የሊዝ መዝገቦች፡-

- ❑ ______________________
- ❑ ______________________

የክፍያ ወረቀቶች፡-

- ❑ ______________________
- ❑ ______________________

የትምህርት ቤት መዝገቦች፡-

- ❑ ______________________
- ❑ ______________________

መግለጫዎች፣ ሂሳቦች፣ ደረሰኞች፡-

- ❑ ______________________
- ❑ ______________________

የሕክምና ሂሳቦች፡-

- ❑ ______________________
- ❑ ______________________

ከገቡበት ቀን ጀምሮ ነዋሪነትን የሚያሳዩ ሌሎች ቀን የተጻፈባቸው ሰነዶች

- ❑ ______________________
- ❑ ______________________

የኢሚግሬሽን መዝገቦች (የሚመለከተው፣ የሚገኝ ከሆነ)፡-

- ❑ *የኢሚግሬሽን ማመልከቻዎች*
- ❑ *የፍርድ ቤት ሂደቶች*
- ❑ *ICE ሂደቶች*
- ❑ ______________________

የአሜሪካ የወንጀል መዝገቦች (የሚመለከተው፣ የሚገኝ ከሆነ)፡-

- ❑ ______________________
- ❑ ______________________

በአሜሪካ ውስጥ በኖሩበት ሁሉም ዓመታት ያሉ የግብር መዝገቦች

- ❑ ______________________
- ❑ ______________________

# ክፍል 6
# *ሌሎች ሰነዶች እና መረጃዎች*

*ቁጥጥር ስር ካዋሉ ምን ማድረግ እንዳለብዎት*

1. *ማንኛውንም የICE ክስተት ለCIRC ሪፖርት ያድርጉ*

2. *እስረኛውን እንዴት ማግኘት እና ማስያዣ መክፈል እንደሚቻል*

3. *ለኢሚግሬሽን ጠበቃ የሚቀርቡ ጥያቄዎች*

4. *በኮሎራዶ ውስጥ ያሉ ጠበቆች*

5. *መብቶችዎን ይወቁ*

6. *የአሜሪካ ፓስፖርት ማመልከቻ*
   *ማስታወሻ፡- ለአሜሪካ ፓስፖርት ብቁ ለመሆን የአሜሪካ ዜጋ መሆን አለብዎት። የተደበላለቀ ሁኔታ ያላቸው ቤተሰቦች የጉዞ የማድረግ ፍላጎት በሚኖርባቸው ጊዜ ብቁ ለሆኑ ሁሉም የቤተሰብ አባላት ፓስፖርቶችን እንዲወስዱ እንመክራለን።*

**ICEን በተመለከተ ማንኛውንም ክስተት ለ CIRCS ኮሎራዶ ፈጣን ምላሽ መስመር ሪፖርት ያድርጉ!**

TU VOZ ES EL PODER
COLORADO TE ESCUCHA

# ማንኛውንም ኢሚግሬሽን የተመለከተ ክስተት ሪፖርት ለማድረግ ወደ 844-864-8341 ይደውሉ!

**American Friends**
**Service Committee (የአሜሪካ ጓደኞች የአገልግሎት ኮሚቴ)**

*የታሰሩ ወዳጅዎን ለመፈለግ፡-*

https://locator.ice.gov/odls/homePage.do

*በስርዓቱ ውስጥ ወዲያውኑ ላይታዩም። ካልታዩ እና ብዙ የአያት ስሞች ካላቸው፣ እያንዳንዱን የስማቸውን ጥምረት ይሞክሩ።*

**American Friends**
**Service Committee**

**በኮሎራዶ ውስጥ የታሰረ ሰው መፈለግ እና መገናኘት**

1) **አንድ ሰው የታሰረበትን ቦታ መፈለግ፡-** ለመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት ግለሰቡ በስርዓቱ ውስጥ የለም። ለ 24 ሰዓታት ከታሰሩ በኋላ የሰውየው ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀን እና የትውልድ አገር ያስፈልግዎታል። የመጀመሪያ፣ የአባት እና ሁሉንም የአያት ስሞች ማግኘትዎን ያረጋግጡ። አንድ ሰው የታሰረበትን ለማወቅ ወደዚህ ይሂዱ፡- https://locator.ice.gov/odls/homePage.doሰውዬው ሁለት የአያት ስሞች ያሉት ከሆነ በመሃል ላይ ሰረዝ ያስገቡ፣ ለምሳሌ፣ Cardenas- Gonzalez። ይህ የማይሠራ ከሆነ፣ በመገልበጥ እና እያንዳንዳቸው ለየብቻ መሞከር አለብዎት።

**የፍርድ ቤት ቀናት፣ የዋስትና መጠኖች እና ቆንስላዎች**

1) **መጪ የፍርድ ቤት ቀናትን ለማወቅ**፣ ወደ 1-800-898-7180 ይደውሉ እና የግለሰቡን የ A ቁጥር ያስገቡ። የኢሚግሬሽን ጉዳዮች ከአገር የመባረር ሂደቶች ላይ ላለ ማንኛውም ሰው የ A ቁጥር ይሰጣል። A 'alien' ማለት ነው።
2) **የአንድን ሰው የዋስትና መጠን ለማወቅ፡-**የሰውየውን የኢሚግሬሽን ዋስትና ለማወቅ ወደ (720) 873-2899 ይደውሉ። ለዚህ የ A ቁጥራቸው ያስፈልግዎታል።
3) **የሰውየውን ቆንስላ ያነጋግሩ፡-** አንዳንድ ጊዜ ይህ አጠቃላይ ጊዜ ማባከኛ ሊሆን ይችላል፣ ግን አንዳንድ ጊዜ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። በማንኛውም ሁኔታ ቆንስላዎ ምን እየሆነ እንዳለ ማወቅ አለበት።

**አንድን ሰው በዋስ ወይም በዋስትና ገንዘብ ማስወጣት**

**የኢሚግሬሽን ዋስትና**
**ቤተሰቡ ሙሉ የዋስትና ማስያዣ መጠን ካለው፡-** <u>ዋስትና የሚከፍለው ሰው በአሜሪካ ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የሚኖር መሆን አለበት።</u>

- ሙሉውን ገንዘብ በገንዘብ ተቀባይ ቼክ ወይም የገንዘብ ትዕዛዝ ውስጥ ማስገባት ያለባቸው ሲሆን የታሰረው ሰው A ቁጥርም በእሱ ላይ መኖር አለበት።
- የገንዘብ ትዕዛዝ ወይም ቼክ ለ Department of Homeland Security (ምህፃረ ቃል አይጠቀሙ) መከፈል አለበት።
- **ዋስትናውን መክፈል የሚችሉት በ** 12445 E. Caley Ave., Centennial, CO ብቻ ነው።
- ኢሚግሬሽን 1-305 የተባለ ቅጽ ወይም ደረሰኝ ይሰጥዎታል። **ይህ ቅጽ** ***<u>ገንዘብዎን ለማስመለስ ያስፈልግዎታል</u>***። ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጡት።

**ሙሉ የገንዘብ መጠን ቢኖራቸው እና ግን በቤተሰብ ውስጥ ማንም ህጋዊ ሁኔታ ከሌለውስ? በቤተሰብ ስም ዋስትና መክፈል እንዴት ይሠራል?**

**<u>ጥንቃቄ!!!</u>**ይህ ኃላፊነት ቤተሰቡ በሚተማመንበት እና ቁርኝት ባለው ሰው መወሰድ አለበት።

**ዋስትና የመክፈል ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?**

ሙሉውን የዋስትና መጠን የሚከፍል ማንኛውም ሰው የወረቀት ሥራውን የማስገባት እና ገንዘቡን ወደ ቤተሰቡ የመመለስ ኃላፊነት አለበት።

- ሰውዬው አድራሻ በሚቀይርበት በእያንዳንዱ ጊዜ ለኢሚግሬሽን እና ለጉምሩክ አስከባሪ (Immigration and Customs Enforcement) ማሳወቅ <u>አለበት</u>። አለበለዚያ ተመላሽ ለማድረግ የሚያስፈልገው የወረቀት ሥራ አይመጣም።
- አንድ ሰው፣ ፍሎር እንበለው፣ በቤተሰቡ ገንዘብ ዋስትና ትከፍላለች፣ ፍሎር ሁሉንም የወረቀት ስራዎች የምትቀበል እና ገንዘቡ ተመላሽ የሚያደርግላት ሰው ነች። ቤተሰቡ የሚተማመንባት ሰው መሆን አለባት። ይህ ማለት ግለሰቡ በመጨረሻ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ቀኖቻቸውን (አንዳንዴ ከዓመታት በኋላ) ሲያጠናቅቁ፣ ቤተሰቡ ዋስትና ከተፈለበት ጊዜ ጀምሮ አሁንም ከፍሎር ጋር መገናኘት አለበት። ፍሎር ገንዘቡ እንዲመለስ የወረቀት ሥራ ለማስገባት እና ገንዘቡን ወደ ቤተሰቡ ለመመለስ ኃላፊነት አለባት።

**ምሳሌ፦** ቤቶ ወንድሙ ፔፔን በዋስትና እንድታወጣ $5,000 ለፍሎር ይሰጣል። ፔፔ በመጨረሻ ከሁለት ዓመት በኋላ ህጋዊ ሁኔታውን ያገኛል። ICE ይህንን ለፍሎር ሊያሳውቅም ላያሳውቅም ይችላል፣ ስለሆነም ፍሎር ስልክዋ እና አድራሻዋ በተለወጠ በእያንዳንዱ ጊዜ ቤቶን ማሳወቅ አለባት። በተጨማሪም ፍሎር አድራሻዋ በተቀየረ ቁጥር ለኢሚግሬሽን እና ለጉምሩክ አስከባሪ (Immigration and Customs Enforcement) መንገር አለባት። ቤቶም ገንዘቡን ማስመለስ ከፈለገ ስልኩ እና አድራሻው በተለወጠ ቁጥር ለፍሎር መንገር አለበት። ፍሎር የዋስትና ማስያዣ ገንዘቡን ለማስመለስ የወረቀት ሥራ ማስገባት እና ከዚያም ወደ ቤቶ መመለስ አለባት። ቤቶ ከፍሎር ጋር ህጋዊ ስምምነት ካልተፈራረመ በስተቀር፣ ገንዘቡን የመመለስ ህጋዊ ግዴታ የለባትም። ለዚህም ነው ግለሰቡ ከቤተሰቡ ጋር መቀራረቡ አስፈላጊ የሆነው።

**የዋስትና ተመላሽ ገንዘብ**

**የእኔ ጉዳይ/የቤተሰቤ ጉዳይ ካለቀ በኋላ የዩኤስ ኢሚግሬሽን ዋስትና ማስያዣ ገንዘብ ተመላሽ እንዴት ማግኘት ይቻላል?**

ግለሰቡ በፈቃደኝነት ከአገር ከወጣ፦

- በፈቃደኝነት ከአገር የወጣበትን ወረቀት ቅጂ ያድርጉ።
- ወረቀታቸውን ለቀው ከወጡበት ቀን በፊት በአገራቸው በሚገኝ የአሜሪካ ኤምባሲ ማስፈረም **<u>አለባቸው</u>**። ኤምባሲው የወረቀት ሥራውን በጊዜው የማይሠራ ከሆነ የተፈረመ የወረቀት ቅጂ መጠየቅ አለባቸው።
- በፈቃደኝነት ከአገር መውጣትን በተመለከተ፣ ከአገር የማስወጣት ትእዛዝ ወይም በእፎይታ የተፈቱ ጉዳዮች፦
- የኢሚግሬሽን ዋስትና ማስያዣ ሲሰረዝ የኢሚግሬሽን እና የጉምሩክ ማስፈጸሚያ፣ የማስፈጸሚያ እና የማስወገድ ስራዎች ፅ/ቤት ዋስትና መሰረዙን ለዕዳ አስተዳደር ማዕከል እና ለግዴታ ተወጪው (ዋስትና ለከፈለው ሰው) በማስታወቂያ - በኢሚግሬሽን ዋስትና መሰረዝ ቅጽ
- (1-391) በኩል ያሳውቃል። ይህንን ቅጽ ከመቀበልዎ በፊት ወራት ሊወስድ ይችላል። **ይህ ቅጽ <u>በጣም አስፈላጊ</u> ነው።** ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጡት።
- ቅጽ 1-391 ሲደርሰው ግዴታ ተወጪው (ዋስትና የከፈለው ሰው) ቅጽ 1-391 እና የDHS ኦፊሴላዊ ደረሰኝ**- ዋናውን-** እንደ ማስያዣ የተወሰደ የዩኤስ ገንዘብ (ቅጽ 1-305 - ICE ዋስትና ሲከፍሉ የሰጥዎትን ቅጽ በሚከተለው አድራሻ ማስገባት አለበት፦

  Debt Management Center
  Attention: Bond Unit
  P.O. Box 5000
  Williston, VT 05495-5000

- **ግዴታ ተወጪው (ዋስትና የከፈለው ሰው) የቅጽ 1-305** (ICE ዋስትና ሲከፍሉ የሰጠዎት ቅጽ) ዋና ከሌለው፣ የተሞላ እና በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ማረጋገጫ በዩናይትድ ስቴትስ የጠፋ ደረሰኝ ICE ለዋስትና እንደ ዋስትና ቅጽ (1-395) ከላይ ለተጠቀሰው አድራሻ መግባት አለበት። ይህ ቅጽ በበይነመረብ በኩል በ፦

http://www.ice.gov/doclib/news/library/forms/pdf/i395.pdf ላይ ይገኛል።

- አግባብነት ያላቸው ቅጾች ለእዳ አስተዳደር ማዕከል ከገቡ እና ከተከናወኑ በኋላ፣ ግዴታ ተወጪው የዋናው የዋስትና መጠን እና በዋስትና ዘመኑ ውስጥ የተጠራቀመ ማንኛውም ወለድ ተመላሽ ያገኛል።

*"የአሜሪካ የኢሚግሬሽን ዋስትና ተመላሽ ገንዘብ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል" ለሚለው ለካቶሊክ የሕግ ኢሚግሬሽን ኔትዎርክ ምስጋና ይግባውhttp://cHnicle%a1.orz/*

**የኢሚግሬሽን ዋስትና**

***ሙሉውን ዋስትና መክፈል ካልቻሉ በዋስትና ሰጪ ድርጅት በኩል ዋስትና መክፈል አለባቸው። የኢሚግሬሽን ዋስትና ማስያዣ ለማግኘት ምን መረጃ ያስፈልገኛል?***

- የታሰረ ሰው ስም
- የሰውዬው የልደት ቀን
- የሰውዬው የትውልድ አገር
- የሰውዬው የA ቁጥር
- የታሰረው ሰው በሚለቀቅበት ጊዜ የሚቆይበት አድራሻ እና ስልክ ቁጥር
- የኢሚግሬሽን ዋስትና ማስያዣ የጠየቀ ሰው ስም (ይህ እርስዎ መሆን የለብዎትም)
- **የኢሚግሬሽን ዋስትና** መጠን

የዋስትና ሰጪው ድርጅት ለግለሰቡ ዋስትና ይከፍላል እናም በ 24 ሰዓታት ውስጥ መለቀቅ አለባቸው። ማህበረሰቡ አብሮ የሰራው አንድ ዋስትና ሰጪ ድርጅት Jeff (ጄፍ) ነው። http://bondsquadbailbonds.com/
720-733-8844. የክሬዲት ካርዶች፣ ጥሬ ገንዘብ እና የመሬት/ቤቶችን መያዣ ቅልቅል ይቀበላሉ።

***ዋሱ ስንት ያስከፍለኛል፣ ለመያዣስ ምን ያስፈልገኛል?***

- ዋስትና ሰጪው እንደኮሚሽናቸው ወይም ክፍያ ከስትናው 15% በላይ ማስከፍል ***የሌባቸውም***፡ ለምሳሌ፣ ዋስትናው $5 5,000 ከሆነ፣ ቤተሰቡ
- $750 ብቻ ቀድሞ መክፈል አለበት።
- ቤተሰቡ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ክፍያ መፈጸም ***<u>የለበትም</u>***፡ ነገር ግን ለሌላው $4,250 (የመኪና ሊብሬ፣ የቤት ባለቤትነት፣ የክሬዲት ካርዶች፣ ጌጣጌጥ፣ ወዘተ) መያዣ መስጠት ብቻ ነው። አንዳንድ የዋስትና ድርጅቶች መሬት ወይም ቤት ያልሆነ ነገር እንደ መያዣ አይቀበሉም።

***<u>ጥንቃቄ፡-</u> የዋስትና ውሉን በጥንቃቄ ያንብቡ።***ኮንትራቱ የሚከተሉትን እንድያደርጉ የሚጠይቅዎት ከሆነ ከዋስትና ድርጅቱ ጋር *<u>መፈራረም የለብዎትም</u>*፡-

- ሙሉ የዋስትና መጠኑን እስኪከፍሉ ድረስ ወርሃዊ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ። ለተቀረው ዋስትና መያዣ ቀድሞውኑ አስይዘዋል። እንዲሁም መልሰው እሱን መክፈል የለብዎትም።
- በማንኛውም መልኩ ወለድ እንዲከፍሉ የሚጠይቅ ከሆነ። የእርስዎ ብቸኛ ግዴታ 15% መክፈል እና መያዣውን ማስያዝ ነው። ምንም ወለድ መክፈል የለብዎትም። በእርግጥ ጉዳይዎ ሲጠናቀቅ የዋስትና ድርጅቱ የዋስትና መጠኑን እና ወለዱን ያስመልሳል እንዲሁም የእርስዎን 15% ይወስዳል!

***ለሌላ ሰው የዋስትና መፈረም ምን አደጋዎች አሉት?***

በዋስትናው ላይ የፈረመ ማንም ሰው ግለሰቡ ፍርድ ቤት ካልቀረበ **ሙሉውን የዋስትና ገንዘብ የመክፈል ወይም ለዋስትና ያስያዘውን *መያዣ* ለዋስትና ድርጅቱ** አሳልፎ የመስጠት ኃላፊነት አለበት። ሰውዬው ሁሉንም የፍርድ ቤት የቀጠሮ ቀናቶቹን ከጨረሰ ከዚያ በኋላ ለዋስትና ድርጅቱ መክፈል ያለበት ምንም ገንዘብ አይኖርበትም።

**ለኢሚግሬሽን ጠበቃ የሚቀርቡ ጥያቄዎች፡-**

1) ህጋዊነትን ለማግኘት ምን እድሎች አሉኝ? ጉዳዬን መከራከር የምንችልባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

2) ከምትሰሩባቸው ጉዳዮች ውስጥ ምን ያህሉ መቶኛ ከእኔ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው?

3) ከእኔ ጋር የሚመሳሰሉ ጉዳዮች ምን ያህል በመቶኛ አሸንፈዋል፣ ለጉዳዬ የመሳካት እድል እንዳለኝ ያምናሉ?

4) በፈቃደኝነት ከአገር መውጣትን ብቀበል ምን ይሆናል? ተመልሶ ለመግባት እንቅፋቶች አሉ? ምን ያህል ጊዜ መጠበቅ አለብኝ? ጉዳዬ የመጽደቁ ዕድል ምን ያህል ነው?

5) ለጉዳዬ ምን ያህል ያስከፍላሉ? ክፍያዎች የሚከፈሉት መቼ ነው? ክፍያዎቹ ምን ምን ይሸፍናሉ? ምንስ አይሸፍኑም?

**ወደ ምክክርዎ ምን ማምጣት አለብኝ።**

1) በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ላለ ማንኛውም የወንጀል ክሶች ሁሉም መዛገቦችዎን

2) ማንኛውም የፈቃደኝነት ሥራ፣ የቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ የስፖርት ቡድኖች፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ተሳትፎ ማረጋገጫ… “የጥሩ ባህሪ” ማስረጃ

3) ማንኛውም የቤተሰብዎ አባል በማንኛውም ጊዜ ለእርስዎ አቤቱታ ካቀረበ ማስረጃ።

4) የቤተሰብዎ አባላት የሆኑ የአሜሪካ ዜጎች እና ቋሚ ነዋሪዎች ዝርዝር

5) እንዴትና መቼ ወደ አሜሪካ እንደገቡ? ከአንድ ጊዜ በላይ ከገቡ፣ ለእያንዳንዱ ጊዜ መቼ እና እንዴት። ስንት ዓመት በአሜሪካ እንደኖሩ?

6) ስለ ቀድሞ ከአገር መባረሮች ወይም ስንት ጊዜ በኢሚግሬሽን እንደታሰሩ መረጃ ለማካፈል ፈቃደኛ ይሁኑ።

## የኮሎራዶ የስደተኛ መብቶች ጥምረት
## የሕግ ባለሙያዎች ዝርዝር

**West Slope (ዌስት ስሎፕ)**

Imelda Mulholland, (Grand Junction) 970-255-8861

Beth Padilla, (Durango) 970-764-4547

**Mountains (ማዉንቴንስ)**

Jennifer Smith, (Glenwood Springs) 970-945-2261

Amy Novak (Vail) 970-306-6476

Karen McCarthy (Dillon) (970) 455-1013

**ዴንቨር**

Chan Law Firm, 303-586-5555

Meyer Law Firm, 303-831-0817

Bethany Immigration Services -970-368-2373

Brooks Immigration, 720-588-3350

Novo Legal Group, 303-335-0250

Cristina Uribe Reyes, 303-317-5516

Christina Brown, 303-747-3494

Lutheran Family Services Rocky Mountain - (303) 389-2337

Catholic Charities - Denver - 303-742-4971

Justice & Mercy Legal Aid Clinic (JAMLAC), 303-839-1008

York Law, LLC., 303-861-3038

David Asser, 602-228-9773

Bryone Heise, 303-495-2013

Jennifer Kain-Rios, 303-455-2125

David Simons, 303-806-0202

Kelly Ryan, 720-917-1060

**Mark Burton, P.C, 303-474-4817**

The Villa Law Firm - (303) 872-9799

**North (ሰሜን)**

Kim Baker Medina (Ft Collins) 970-308-1184

Immigrant Roots Law Office (Longmont) 720-815-2900

Immigrant Legal Center of Boulder County (Boulder) 303-444-1522

Ronquillo Immigration Law (Boulder) 970-400-7007

Lisa Green & Associates (Boulder) 303-444-9500

CU Law Clinic (Boulder) 303-492-5830

Steele-Kaplan Law (Loveland & Greeley) 970-461-1282

Christina Brown (Fort Morgan) 970-370-2575

David Hall (Loveland) 970-599-1263

Francesca Ramos, (Longmont) 303-417-6370

The Saltrese Law Firm, (Boulder) 303-442-8554

Emily Smith, (Erie) 720-630-4429

**South (ደቡብ)**

Pikes Peak Immigration (Colorado Springs) 719- 602-4477

Izaguirre Law Firm, (Colorado Springs & Pueblo) 719-445-0292

Joseph Law Firm, PC., (Colorado Springs) 303-297-917

Hanes & Bartels, LLC (Colorado Springs) (719) 260-7900

Deere Law, LLC (Colorado Springs) 719-633-3377

Wilkens Law (Colorado Springs)

Murphy & Price, LLP (Colorado Springs)

Daugherty Law (Colorado Springs)

**Family Legal Orientation Program (የቤተሰብ የህግ መረጃ ፕሮግራም)**

**Rocky Mountain Immigrant & Advocacy Network,** 720-543-8898

(ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወጣቶች እና በእስር ቤት ውስጥ ላሉ ሰዎች ነጻ)

## መብቶችዎን ይወቁ፡- **ወሳኝ ቃላት**

1) "ስህተት ሰርቻለሁ?"
2) "ለመሄድ ነፃ ነኝ?"
3) "ፍተሻ አልፈቅድም!"
4) "አልናገርም!"
5) "ጠበቃዬን ማናገር እፈልጋለሁ!"
6) "ፍርድ ቤቶች ዋስትና ከፈቀዱ…የመክፈል መብት አለኝ። "
7) "የማዘዣ ወረቀት ማየት እፈልጋለሁ።"

# ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ ICE ወደ ቤትዎ ቢመጣ

## በር አይክፈቱ

ICE የወንጀል ፍርድ ቤት ዳኛ ትዕዛዝ ሳይይዝ ወደ ቤት መምጣት አይችልም። ሊገቡ የሚችሉት እርስዎ ከፈቀዱላቸው ብቻ ነው።

## ዝም ይበሉ

ICE በኢሚግሬሽን ጉዳይዎ ላይ የሚናገሩትን ማንኛውንም ነገር ሊጠቀም ይችላል፣ ስለዚህ ዝም የማለት መብትዎን ይጠይቁ!

*እንዲ ይበሉ "በአምስተኛው የህግ ማሻሻያ መሰረት ያለኝን ዝም የማለት መብቴን ለመጠቀም እመርጣለሁ።

## አይፈርሙ

ICE በኢሚግሬሽን ጉዳይዎ ላይ የሚናገሩትን ማንኛውንም ነገር ሊጠቀም ይችላል፣ ስለዚህ ዝም የማለት መብትዎን ይጠይቁ!

## ሪፖርት ያድርጉ እና መዝገበው ይያዙ!

ወዲያውኑ ሪፖርት ያድርጉ፡- የ UWD መስመር 1-844-363-1423.

በፌዴራል መንግስት ንብረት ላይ ካልሆኑ በስተቀር ፎቶዎችን እና ቪዲዮዎችን ይቅዱ።
ባጅ ቁጥሮች፣ የወኪሎች ብዛት፣ ጊዜ፣ የመኪና አይነት እና በትክክል ምን እንደተከሰተ ማስታወሻዎችን ይውሰዱ!

## ይፋለሙ!

የታመነ ጠበቃ ይፈልጉ እና ጉዳይዎን ለመከራከር ሁሉንም አማራጮች ያስሱ። ከታሰሩ፣ ዋስትና ሊያገኙ ይችላሉ - ተስፋ አይቁረጡ! እራስዎን ከህግ አስከባሪ እርምጃ ለመከላከል የአካባቢዎን ቡድን ይቀላቀሉ!

unitedwedream.org/end

United We Dream